# የደወል ጊዜያት ማሳሰቢያ
# አጠቃላይ ሃሳብ

Montgomery County Public Schools (MCPS) የትምህርት ቤቶችን መጀመሪያና መጨረሻ ጊዜያት- የደወል ጊዜያት በመባል የሚታወቀውን- መለወጥ/ማሻሻልን እያሰበበት ሲሆን ይህም ተማሪዎች በተለይም የሁለተኛ ደረጃ ትም/ቤት ተማሪዎች በቂ ዕንቅልፍ እንዲያገኙ ለመርዳት ነው። የትም/ቤቶች የበላይ ሃላፊ (ሱፐርኢንቴንዳንት) Joshua P. Starr (ጆሹኣ ፒ. ስታር) ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትም/ቤት ከ50 ደቂቃ በኋላ እንዲጀምር፣ መካከለኛ ደረጃ ትም/ቤት 10 ደቂቃ ቀደም ብሎ እንዲጀምር እና የኤለሜንታሪ ትም/ቤት መጀመሪያ ጊዜያት ሳይለወጥ እንዲቀጥል ነገር ግን ቀኑን በ30 ደቂቃ ለማራዘም ማሳሰቢያ አቅርቧል። ኦክቶበር 8 2013 Montgomery County Board of Education (የትምህርት ቦርድ) የDr. Starr (ዶ/ር ስታር) ፕላንን በመደገፍ ድምፅ የሰጠ ሲሆን ይህም ከማህበረሰቡ ሰፊ ግብአት (input) ለማሰባሰብ እናም ወጪንና የለውጡ ማሻሻያ ሃሳብ በስራ ላይ የሚያደርሰውን ውጤት ለማጥናት ነው። ማንኛውም የደወል ጊዜያት ለውጥ ለደረግ የሚችልበት ጊዜ እጅግ በጣም ከፈጠነ በ2015-2016 የትምህርት አመት ነው።

**የደወል ጊዜያት የስራ ቡድን**

የዶ/ር ስታር (Dr. Starr) ማሳሰቢያ መሰረት ያደረገው የ2013 የደወል ጊዜያት የስራ ቡድን ዘገባን ነው። ቡድኑ ዲሴምበር 2012 የተመሰረተና ጉዳዩን የሚመለከቱ ያለፉ ዘገባዎችን በማጥናት፣ ወቅታዊ ምርምርን በመመልከት፣ ከባለሙያዎች በመስማት እና ዶ/ር ስታር (Dr. Starr) ሊያገናዝባቸው የሚችሉ አማራጮችን በማዳበር ወራትን አሳልፏል። ዘግይቶ መጀመር ጊዜያትን በተመለከተ በቂ ፍልጎት ካለ ለመወሰን ቡድኑ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎችንና ወላጆቻቸውን ያካተተ ቅኝቶች አድርጓል። ኦገስት 2013 ዶ/ር ስታር (Dr. Starr) የቡድኑ ዘገባ የደረሰው ሲሆን ዘገባው በአስሮች እድሜ ውስጥ ያሉ ሰዎች የመተኛት ፍላጎትን የሚመለከቱ የምርመር ግኝቶችና ትምህርት የመጀመሪያ ጊዜያትን በተመለከተ ሌሎች ምርምሮችን አጠቃሎ ያቀረበ ነው። የዘገባው ቁልፍ ግኝቶች የሚከተለውን ያካትታሉ፡

- ተማሪዎች ወደ አስሮች እድሜ ውስጥ ሲደርሱ ሰውነታቸው የሚለወጥ ሲሆን ይህም ከዚህ በፊት በነበራቸው የወጣትነት እድሜ ያደርጉ እንደነበረው በጊዜ መተኛት አይችሉም፣ ነገር ግን ከአዋቂዎች የበለጠ የመተኛት ፍላጎታቸው ይቀጥላል።
- በአገር አቀፍ ደረጃ ጥናቶች እንደሚያሳዩት በአስሮች እድሜ ያሉ በአንድ ሌሊት ከ8.5 እስከ 9.5 ሰአት መተኛት ይፈልጋሉ፣ ነገር ግን በአማካኝ 7.6 ሰአት ያገኛሉ። ልክ እንደታተመው ምርምር ሁሉ በስራ ቡድኑ የተደረጉት የMCPS የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ቅኝቶች ያሳዩት የMCPS ሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች በአንድ ሌሊት ወደ ሰባት ሰአት አንዳድ ጊዜም ከዚያ ያነሰ ይተኛሉ።
- የእንቅልፍ ማነስ የመማር ሂደት አካል የሆኑበትን የአእምሮ ስራዎች ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ያለው ሲሆን ይህም በቀን የተማሩትን መረጃ የማሰባሰብና ማስታወስ ችሎታ፣ የትውስታ ተግባራትን እና ከፍተኛ የአእምሮ ስራ የሚያስፈልጋቸውን ረቂቅና ውስብስብ ተግባርን ያካትታል።
- በአስሮች እድሜ ያሉ ልጆች እንቅልፍ ማነስ ከከፍተኛ የሰውነት ክብደት መጨመርና ጭንቀት፣ ዝቅተኛ ደረጃ ተነሳሽነትና ትኩረት እናም እየጨመረ ካለው የትራፊክ አደጋዎች ጋር የተዛመደ ነው።
- ትምህርት ቤቶች የመጀመሪያ ጊዜያትን ሲያዘገዩ ምርምር እንደሚያሳየው በአስሮች እድሜ ያሉ ብዙ ይተኛሉ እናም በኋላ ዕንቅልፍ በማጣት ንቁ ሆነው አይቆዩም፣ ብዙውን ጊዜ እንደተገመተው።
- ትምህርት ቤቶች የመጀመሪያ ጊዜያትን ሲያዘገዩ ምርምርም እንደሚያሳየው በአስሮች እድሜ ያሉ ሹፌሮች ለጥቂት የአውቶሞቢል (መኪና) አደጋዎች ይጋለጣሉ።
- የ2013 MCPS ቅኝት እንዳሳየው የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ወላጆች 70 ፐርሰንት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት የሚጀምረው "በጣም ቀድሞ" እንደሆነ የተሰማቸው ሲሆን 69 ፐርሰንት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት መጀመሪያ እንዲዘገይ ፈልገዋል። በዚያው ተመሳሳይ ቅኝት እንደተገኘው 63 ፐርሰንት የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት የሚጀምረው "በጣም ቀድሞ" እንደሆነ የተሰማቸው ሲሆን 54 ፐርሰንት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት መጀመሪያ እንዲዘገይ መፈለጋቸውን አመልክተዋል።

ዶ/ር ስታር (Dr. Starr) ከግምት ውስጥ እንዲያስገባ የደወል ጊዜያት ስራ ቡድን በርካታ አማራጮችን አቅርቧል። እንዲሁም ዲስትሪክቱ ተማሪዎችንና ወላጆችን ስለ ዕንቅልፍ አስፈላጊነትና የዕንቅልፍ እጦት የሚያስከትለውን አደጋ በተመለከተ የማስተማር እርምጃ እንዲጀምር የስራ ቡድን አሳስቧል።

**የትምህርት ቤቶች ሃላፊ (ሱፐርኢንቴንደንት) ማሳሰቢያ**

**በአሁኑ ወቅት የMCPS ደወል ጊዜያት ክፍለ ጊዜ የሚከተለው ነው፡**

| ደረጃ | ሰዓት | የቀኑ ቆይታ/ርዝመት |
|---|---|---|
| ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት | 7፡25 a.m. - 2፡10 p.m. | 6 ሰአት፣ 45 ደቂቃ |
| መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት | 7፡55 a.m. - 2፡40 p.m. | 6 ሰአት፣ 45 ደቂቃ |
| ኤለሜንታሪ ትምህርት ቤት ታየር 1 | 8፡50 a.m. - 3፡05 p.m. | 6 ሰአት፣ 15 ደቂቃ |
| ኤለሜንታሪ ትምህርት ቤት ታየር 2 | 9፡15 a.m. - 3፡30 p.m. | 6 ሰአት፣ 15 ደቂቃ |

**በዶ/ር ስታር (Dr. Starr) ማሳሰቢያ የደወል ጊዜያት ክፍለ ጊዜ ንድፈ ሃሳብ የሚከተለው ነው፡**

| ደረጃ | ሰዓት | የቀኑ ቆይታ /ርዝመት |
|---|---|---|
| ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት | 8፡15 a.m. - 3:00 p.m. | 6 ሰአት፣ 45 ደቂቃ |
| መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት | 7፡45 a.m. - 2፡30 p.m. | 6 ሰአት፣ 45 ደቂቃ |
| ኤለሜንታሪ ትምህርት ቤት ታየር 1 | 8፡50 a.m. - 3፡35 p.m. | 6 ሰአት፣ 45 ደቂቃ |
| ኤለሜንታሪ ትምህርት ቤት ታየር 2 | 9፡15 a.m. - 4፡00 p.m. | 6 ሰአት፣ 45 ደቂቃ |

**ተጨማሪ ዝርዝር በሚከተለው ጠቋሚ ድረ-ገጽ የደወል ጊዜያት 2013 ዘገባ ሊገኝ ይችላል፡**

www.montgomeryschoolsmd.org/info/belltimesworkgroup/index.aspx

**ማህበረሰብን ማሳወቅ/ማሳተፍ እና የወደፊት ትንተና**

የዚህ ሂደት ቀጣይ ደረጃ ሆኖ የተቀየሰው የዶ/ር ስታር (Dr. Starr) ማሳሰቢያን በሚመለከት ተማሪዎችን፣ መምህራንን/ሰራተኞችን፣ ወላጆችን እና ማህበረሰቡን በሰፊው በማሳተፍ ግብአት ማሰባሰብ ነው። ማህበረሰቡን ማሳተፍ የሚያካትተው አራት የህዝብ ስብሰባዎች፣ ከማህበረሰቡ ድርጅቶች ጋር የሚኖሩ ስብሰባዎች፣ ቅኝቶች፣ ለጉዳዩ ትኩረት የሚሰጥ ቡድን ውይይትና ግብአት የሚያበረክቱ ሌሎች እድሎችን ነው። ዶ/ር ስታር (Dr. Starr) ብዙውን ጊዜ በህዝብ ስብሰባዎችና ውይይቶች የማይሳተፉትን ጨምሮ መላ ማህበረሰቡን በስብሰባ የማሳተፍን አስፈላጊነትን ትኩረት ሰጥቶታል። ምንም እንኳን ወጪን በሚመለከት የቅድመ ግምት በየደወል ጊዜያት ስራ ቡድን ዘገባ አካል ሆኖ የቀረበ ቢሆንም ወጪና በተግባራዊነት ወቅት በትምህርት ቤት ክፍለ ጊዜ ሚያስከትለውን ለውጥ በሚመለከት ዝርዝር ትንተና እንዲሚላ ያስፈልጋል።

ዶ/ር ስታር (Dr. Starr) እና የትምህርት ቦርድ (Board of Education) የስራ ክፍለ ጊዜ፣ ልጅ የማስጠበቅ አደረጃጀትና የቤተሰብ የዕለት ከዕለት ተግባር ሊታወክ እንደሚችል ተገንዝበዋል፤ ስለዚህ የጊዜ ሰሌዳው እያንዳንዱ ግብአት የሚያደርግበት ጥሩ ዕድልና የታሰበውን ለውጥ በመመስረት ዕቅድ ለማውጣት የሚያስችል ነው። ምንም እንኳን ለስራ ቡድኑ መመስረት ምክንያት የሆነው የወቅቱ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች የመጀመሪያ ሰአት 7፡25 a.m. መሆኑ ቢሆንም መካከለኛና ኤለሜንታሪ ተማሪዎችና ቤተሰቦቻቸው እንዲሁም በሁሉም የትምህርት ደረጃዎች ያሉ መምህራንና ሌሎች የMCPS ሰራተኞች በትምህርት የደወል ጊዜያት ለውጦች ላይ የሆነ ለውጥ እንዲደረግ ከፍተኛ ፍላጎት ያላቸውና ሊደመጡ የሚገባ ነው።

ዘግይቶ የመጀመር ጊዜ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ጤንነትና ደህንነት ላይ የሚኖረው ጥቅም ከፍተኛና በሰፊው ሊታይ የሚገባ ነው። ሌሎች ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት/ሽርካዎች በእነርሱ ዘንድ የሚያስከትለው ውጤት እንዴት እንደሚሆንና ልጆች በአካዴሚያዊ ሙያቸው በMCPS ሲገሰግሱ ምን ጥቅሞችና ፈተናዎች/መሰናክሎች እንደሚከሰቱ መረዳት ሊፈልጉ ይችላሉ።

MCPS
ROCKVILLE, MARYLAND

## አጠቃላይ ጉዳዮች ለኤለሜንታሪና መካከለኛ ትምህርት ቤቶች

*ኤለሜንታሪ ት/ቤት*

የኤለሜንታሪ ትም/ቤት ማህበረሰቦች በጥቅሉ ሲታይ የትምህርት ቀን አሁን ካለው ዘግይቶ እንዲጀመር አይፈልጉም። እንዚህን ፍላጎቶች ለመጠበቅ የቀረበው ንድፈ ሃሳብ የኤለሜንታሪን መጀመሪያ ሰአትን አይለውጥም ነገር ግን የተማሪን ቀን በ30 ደቂቃ ያራዝማል። የስራ ቡድኑ ተጨማሪ የጠዋት ልጅ ጥበቃ ፍልጎት ሊፈጥር የሚችልን ማንኛውንም የኤለሜንታሪ መጀመሪያ ሰአት ማዘግየትን ለመከላከል ይፈልጋል።

- MCPS የኤለሜንታሪ ትምህርት ቀን በሜሪላንድ ውስጥ ከአንድ ዲስትሪክት በስተቀር ከሁሉም ያነሰ/ያጠረ መሆኑ ለተወሰነ ጊዜ ሲያሳስበው ነበር። የኤለሜንታሪ ተማሪዎችና መምህራን ከተጨማሪ መማሪያ ጊዜ ሊጠቀሙ ይችላሉ። ተጨማሪ ጊዜውን እንዴት መጠቀም እንደሚቻል በቀጣይ በርካታ ወራት አንዱ የመወያያ ክፍል ሊሆን ይችላል።
- መካከለኛ፣ ከፍተኛ እና ኤለሜንታሪ ትምህርት ቤቶች በ30 ደቂቃ ልዩነት እንዲጀምሩ ለማድረግ፣ ማንኛውም ትምህርት ቤት ከ7፡45 በፊት ወይም ከ9፡15 a.m. በኋላ ያለመጀመሩ ሲሆን፣ የአውቶብስ አጠቃቀምን ከፍ ለማድረግ በእያንዳንዱ ደረጃ የትምህርት ቀን ቆይታ/ርዝመት ተመሳሳይ እንዲሆን ያስፈልጋል።

*መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት*

በማሳሰቢያው መሰረት መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ10 ደቂቃ ቀደም ብሎ ይጀምራል። ይህ ለውጥ ያስፈለገው የኤለሜንታሪ ትምህርት ቤቶች ዘግይቶ መጀመርን ለማስወገድ፣ የትምህርት ቤት አውቶብሶች በቂ ጊዜ ኑሯቸው ሁሉንም ትምህርት ቤቶችን እንዲያገለግሉና የሚያደርጉትን ጉዞ እንዲፈጽሙ ነው። አብዛኛው የMCPS አውቶብሶች ጠዋትና ከሰአት በኋላ ባለው ጊዜ ሶስት ወይም አራት ትም/ቤቶችን ያገለግላሉ።

- የደወል ጊዜያትን በተመለከተ በተደረጉ የማህበረሰብ ውይይቶች የወላጆችና መምህራን ተሳትፎ ምላሽ እንደሚያመለክተው አብዛኛው ተሳታፊዎች ትምህርት ቤቶች በ8፡00 a.m. አካባቢ እንዲጀምሩ ይፈልጋሉ። የትምህርት ቤቶች የበላይ ሃላፊ (ሱፐርኢንቴንዳንት) ንድፈ ሃሳብ አማራጭ እጅግ የበለጠ የመጓጓዣ መገልገያዎችን አጠቃቀም የሚፈጥር ሲሆን ለሁሉም መካከለኛ ትም/ቤቶችና ሁለተኛ ደረጃ ትም/ቤቶች የመጀመሪያ ሰአታት በተቻለ መጠን ወደ 8፡00 a.m. የተጠጋ መሆንን የሚጠብቅ ነው።
- መካከለኛ ትም/ቤቶች ከሁሉም በጣም ቀድመው የመጀመሪያ ጊዜ እንዲኖራቸው የተመረጠበት ምክንያት በእንቅልፍ ምርምር መሰረት ተደርጎ ሲሆን ወጣት የመካከለኛ ትም/ቤት ተማሪዎች (በተለይ 6ኛና 7 ክፍል ተማሪዎች) ከኤለሜንታሪ ተማሪዎች ጋር በእንቅልፍ ፍላጎቶች በጣም ተመሳሳይ እና ከሁለተኛ ትም/ቤት ተማሪዎች ቀድመው በጊዜ መተኛት እንደሚችሉ የሚያመለክት ነው። በእድሜያቸው ከፍ ያሉ የመካከለኛ ትም/ቤት ተማሪዎች (በተለይ 8ኛ ክፍል ተማሪዎች) የእንቅልፍ ፍላጎታቸው ከሁለተኛ ደረጃ ትም/ቤት ተማሪዎች በጣም ተመሳሳይ ነው፤ ይሁን እንጂ የስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች እንደ ሁለተኛ ደረጃ ትም/ቤት ተማሪዎች ሙሉ አካዴሚያዊ እና መደበኛ ያልሆነ ትምህርት ጫና የለባቸውም። ስለዚህ ይህ የ10 ደቂቃ የመጀመሪያ ሰአት ማስተካከያ በመካከለኛ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ላይ አነስተኛ ተፅዕኖ እንደሚያስከትል ይጠበቃል።
- እያንዳንዱ የደወል ጊዜያት ውይይት የሚያካትተው የማግኘት-ማጣት ማቻቻል (trade-offs) እንዳለው መታወቅ ያለበት ሲሆን፤ ማህበረሰቡ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ለአራት አመት የመጀሪያ ሰአት በ8፡15 a.m. የመሆንን ጥቅም ከመካከለኛ ትምህርት ቤት በ10 ደቂቃ ቀድሞ ከመጀመር ጋር መለወጥን ከግንዛቤ እንዲያስገባ ይጠየቃል። ይህ ለውጥ የሚያስከትለው ተፅዕኖን ለመወሰንና የሚጠበቁትን ፈተናዎች/መሰናክሎች የሚያስወግዱ ዘዴዎችን ለመፈለግ የመካከለኛ ትምህርት ቤት ከሚመለከታቸው አካላት/ሽርካዎች ግብአት ማግኘት ይኖራል።

በሰፊው የማሳወቅ/የማሳተፍ ፕላን በሁሉም ደረጃዎች ያሉትን ተማሪዎች፣ ወላጆች እና መምህራን እንዲሁም በለውጡ ተጽዕኖ ሊደርስባቸው የሚችሉ የንግድ (ቢዚነስ) ማህበረስብና የአካባቢ ተቋማትን የሚያሳትፍ ይሆናል። አንዴ ሁሉም ግብአት ከተገኘና ሙሉ ወጪው ከተወሰነ በኋላ የመጨረሻ ማሳሰቢያ ይዘጋጅና ከMontgomery County Board of Education (ትምህርት ቦርድ) ጋር በመጨረሻው የስፕሪንግ ወቅት 2014 ውይይት ይካሄዳል።

MCPS
ROCKVILLE, MARYLAND
0567.14 • AMHARIC • EGPS